በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 235741

ቀን ፡- ጥቅምት 27 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካቾች ፡- 1. ወ/ሮ እልፍነሽ ገ/ኪዳን ------ 2ኛ አመልካች ቀረቡ

2. ወ/ሮ አበባ አማረ ----- ቀረቡ

3. አቶ ሚሊዮን አማረ
4. ወ/ሮ ሙሉመቤት አማረ
5. ወ/ሮ አዳነች አማረ
6. አቶ ጥዑም በርሔ
7. አቶ ብርሀኔ አስመላሽ

} ወኪል 2ኛ አመልካች ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡- 1. ወ/ሮ ፀሐይ በቀለ ቦካን ሞግዚት እና አሳዳሪ አድራጊያቸው

ሀ/ ህጻን ቃልኪዳን ፍሰሀ አማረ

ለ/ ህጻን ሚካኤል ፍሰሀ አማረ

ሐ/ ህጻን ናታኒም ፍሰሀ አማረ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## <u>ፍርድ</u>

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያጸናው እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገቦች፤ ተጠሪዎች አመልካቾች ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪዎች ጥቅምት 12 ቀን 2019 ዓ/ም ባቀረቡት አቤቱታ የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት እና ከ2ኛ-4ኛ ያሉት ተጠሪዎች ወላጅ አባት የሆኑት አቶ ፍሰሀ አማረ ተክሌ ጥር 25 ቀን 2008 ዓ/ም ስላረፉ ውርስ አጣሪ ተሹሞ ውርስ እንዲጣራላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ከ1ኛ-5ኛ ያሉት አመልካቾች ጥር 17 ቀን 2009 ዓ/ም ባቀረቡት አቤቱታ የሟች እናት፣ ወንድሞች እና እህቶች መሆናቸውን በመግለጽ፤ ውርሱ በአግባቡ ስላልተጣራ በክርክሩ ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩ እና ገለልተኛ ውርስ አጣሪ እንዲሾምላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ 6ኛ እና 7ኛ አመልካቾች እንደ ቅደም ተከተላቸው ለዕቁብ ብር 275,000 እና 135,000 ከፍለው፤ ሟች የዕቁቡ ጸሐፊ እና ገንዘብ ሰብሳቢ ሆነው የተሰበሰበ ገንዘብ እና ቼክ በእሳቸው እጅ ስለሚገኝ ዕጣው ሳይደርስቻው ዕቁቡ ስለተበተነ በውርስ ዕዳነት እንዲያዝላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ለመጨረሻ ጊዜ ሚያዚያ 07 ቀን 2013 ዓ/ም ተሻሽሎ የቀረበውን የውርስ አጣሪ ሪፖርት መሰረት በማድረግ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲሰጡበት አዟል፡፡ በዚሁ መሰረት አመልካቾች ግንቦት 16 ቀን 2013 ዓ/ም ተጽፎ በሰጡት አስተያየት የውርስ ሀብት በሆነው ቤት እና ይዞታ ላይ የወራሾች ድርሻ ሲገለጽ የሚያሻማ በመሆኑ ወራሾች 1/5ኛ ድርሻ አላቸው እንዲባልላቸው ጠይቀዋል፡፡ ጣልቃ ገቦች በበኩላቸው አስተያየታቸውን በጊዜ ስላልሰጡ ሚያዚያ 28 ቀን 2013 ዓ/ም እና ሰኔ 01 ቀን 2013 ዓ/ም መብታቸው ታልፏል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን እንደመረመረው 5 ክፍል ቤቶች በተመለከተ በተጠሪዎች በኩል የቀረቡ ምስክሮች ሟች ቤቶቹን ሲያሠሩ እንደነበረ እና የሚያሠሩትም በእራሳቸው ለእራሳቸው መሆኑን ሟች እንደነገሩዋቸው ነው፡፡ በመሆኑም በዋናነት የምስክሮች ቃል መሰረት ያደረገው ሟች ነገሩን የሚሉትን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሟች በእራሳቸው ገንዘብ በሌላ ሰው ይዞታ ላይ ለእራሳቸው ቤት መሥራታቸውን በበቂ ሁኔታ የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል የጣልቃ ገብ ምስክሮች እራሳቸው ጣልቃ ገቦች ቢሆኑም ተቀራራቢ በሆነ ሁኔታ ሟች ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ክፍሎች ሟች ኃላፊነት በመውሰድ በእናታቸው ገንዘብ ከሌላ ወንድማቸው ጋር በመሆን እንዳሠሩ መስክረዋል፡፡ ስለሆነም 5 ክፍል ቤቶች የውርስ ንብረት ናቸው የሚያስብል አይደለም፡፡ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ውስጥ የሚገኘው የቤት ቁጥር 109 የሆነው ቤት እና ይዞታ ላይ ሟች በእራሳቸው ገንዘብ በሌላ ግለሰብ ይዞታ ላይ ለእራሳቸው ቤት መሥራታቸውን የፍ/ብ/ህ/ቁ 1178 እና 1179 በሚያስቀምጠው ሁኔታ ስላላረጋገጡና ክፍሎቹ ሟች የግል ንብረት መሆናቸው ስላልተረጋገጠ በውርስ ንብረትነት ሊያዝ አይገባም፡፡ በመሆኑም በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ውስጥ የሚገኘው የቤት ቁጥር 109 የሆነው ቤት እና ይዞታ ግማሹ ድርሻ የ1ኛ አመልካች፣ ግማሹ ድርሻ ሟችን ጨምሮ ከ2-5 ያሉ አመልካቾች እኩል 1/5ኛ ድርሻ፣ የሟች 1/5ኛ ድርሻ ደግሞ እኩል ከ2ኛ-4ኛ ላሉ ተጠሪዎች ሊከፋፈል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የ6ኛ እና 7ኛ አመልካቾችን ጥያቄ በተመለከተ ሟች የዕቁብ ገንዘቡን የሰበሰቡ እና ለእራሳቸው የወሰዱት ስለመሆናቸው በውርስ አጣሪም ሆነ በችሎት ትዕዛዛ የቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች የሉም፤ በመሆኑም በውርስ እዳነት እንዲያዝላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ ከዚህ ውጪ የውርስ ሪፖርቱ በአግባቡ የተጣራ፣ በማስረጃ የተረጋገጠ እና የሚነቀፍ ሆኖ ስላልተገኘ ጸድቋል፤ ከ2ኛ-4ኛ ያሉ ተጠሪዎች የወራሽነት ማስረጃ ይሰጣቸው በማለት ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን የይግባኝ አቤቱታ ባለመቀበል ሰርዟል፡፡

ይሕ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ አመልካቾች ጥምቅት 08 ቀን 2015 ዓ/ም በጻፉት የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች የፈጸሙትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ለማስለወጥ የቀረበ ነው፤ 1ኛ አመልካች በገንዘባቸው ማንም ሳይቃወማቸው በጋራ ይዞታው ላይ የሠሩትን የግላቸውን ቤት የግል ነው በማለት ውሳኔ መስጠት ሲገባው የውርስ ሀብት ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል፡፡ ግሮሰሪው ውስጥ የሚገኙትን ንብረቶች አስመልክቶ የውርስ አጣሪ ያካተተው ሀሳብ ትክክል አለመሆኑን እየገለጽን፣ አስተያየት እንድንሰጥ እየጠየቅን፣ በችሎቱ የቀጠሮ ማሳሳት አስተያየት እንዳንሰጥ የተደረግን መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት እየተቻለ፤ በአመልካቾች የቀረበውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃ ሳይመረምር ወይም ንብረቶቹ በአመልካቾች እጅ መኖራቸውን ተጠሪዎች በማስረጃ ባላረጋገጡበት ሁኔታ በ1ኛ አመልካች ንግድ ቤት ውስጥ ያሉትን ንብረቶች የሟች ንብረቶች ናቸው በማለት የውርስ አጣሪ ሪፖርቱን ማጽደቁ፤ በተጨማሪም የእኚህን ንብረቶች መጠን በግልጽ ሳይለዩ የጸደቀውን የውርስ አጣሪ ሪፖርት በውሳኔ ማጽደቁ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ የዕቁብ ገንዘብን አስመልክቶ ሟች የዕቁብ ገንዘብ የወሰዱ እና ከወሰዱ በኂላ ግን ለወሰዱት ገንዘብ ተመጣጣኝ ክፍያ በዕቁብ ደንብ መሰረት ያልከፈሉ መሆኑን በእጅ ጽሑፋቸው እና በፊርማቸው የተረጋገጠ የዕቁብ መዝግብ፣ የዕቁብተኞች ደብተር እና የባንክ መረጃ እና ልዩ ልዩ ሰነዶች በማስረጃነት ቀርበው እያለ እና ተጠሪዎች ባላስተባበሉበት በውርስ ዕዳነት ሊያዙ የሚገቡ ሆነው አልተገኙም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በዚህ ፍርድ ቤት እንዲታረምልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ በፍርድ ሀተታው ውስጥ በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 06 ውስጥ የሚገኙ በግል የተሠሩ ቤቶችን ለይቶ ካስቀመጠ በኂላ በውሳኔ ክፍል ውስጥ የግል ቤቶችን በተራ ቁጥር 2 እና 3 ስር ደግሞ በዚሁ ቤት ውስጥ የሚገኙት ቤቶች ሁሉም የውርስ ሀብት ናቸው መባሉ የፍርድ እና የውሳኔ አለመጣጣም እና ለአፈጻጸም አስቸጋሪ አይሆንም የሚለውን ተያያዥ ጉዳይም ለማጣራት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡

ተጠሪዎች ታህሳስ 18 ቀን 2015 ዓ/ም በተጻፈ ያስቀርባል ተብሎ በተያዘው ጭብጥ ላይ የሰጡት የመከላከያ መልስ የቤት ቁጥር 109 1ኛ አመልካችና ሟች አቶ አማረ ተክሌ በጋብቻ አብረው በነበሩበት ጊዜ የተሰራ ቤት በመሆኑ ከ2ኛ-5ኛ ያሉት ተጠሪዎች ወላጅ አባታቸው ከአባታቸው በውርስ ያገኙት ቤት በመሆኑ ከውርስ ድርሻው 1/5ኛ ድርሻ አላቸው ተብሎ በተወሰነው መሠረት ተጠሪዎች ከዚህ ቤት ላይ አባታቸውን

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በመተካት የአቶ አማረ ተክሌን ድርሻ ወራሽ ናቸው፡፡ የተጠሪዎች አባት በግቢው ውስጥ በተሠራው ሰርቪስ ቤት የኮካ-ኮላ እና አምቦ ውሃ የማከፋፋል ንግድ ሥራ ሲሠሩ የነበሩ ናቸው፡፡ ሟች የግንባታ ፈቃድ በስማቸው ከመውጣታቸው በተጨማሪ ቤቶቹን የገነቡት እና በተለይም በግቢው የሚገኘው ዋናውን የውርስ ቤት አያታቸው ከሞቱ በኋላ የውርስ ሀብቱ ያልተከፋፈለ ከመሆኑም በላይ ይህ የውርስ ቤት ሳይከፋፈል ክፍሎቹን በማከራየት የተገኘው ገቢ ያልተካፈለ በዚህ ገቢ ሰርቪሶቹ የተሰሩ በመሆኑ የውርስ ሀብት ናቸው፡፡ ቤቶቹ የተሰሩት በሟች ሀብት ነው በማለት የስር ፍድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍበት የህግና የማስረጃ ስህተት ስለሌለ አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ እንዲያፀናልን እንጠይቃለን፡፡ የኮካ-ኮላ እና አምቦ ውሃ ማከፋፈያ ግሮሰሪ የነበራቸው ሲሆን ስንት ሳጥን ኮካና አምቦ ውሃ ለጅምላ ንግዳቸው ይጠቀም እንደነበር፣ የኮካ-ኮላ እና አምቦ ውሃ አምራች ድርጅቶቹ ጋር ውል ሲዋዋል የተፈራረመበትን ማስረጃ ለውርስ አጣሪው አቅርበን ማስረጃው በፋይሉ ተያይዟል የውርስ አጣሪው ፋይልም ከመጀመሪያ ፍርድ ቤቱ ፋይል ጋር ተያይዞ ስለሚገኝ፤ ከተጠሪዎች መጠኑ ተጠቅሶ የቀረበውን የተቀበለው ስለሆነ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማጽናት መዝገቡን ዘግቶ እንዲያሰናብተን በማክበር እናመለክታለን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች ጥር 05 ቀን 2015 ዓ/ም ባቀረቡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪዎች ያቀረቡት የክስ አቤቱታ የሟች አቶ ፍስሃ አማረ የውርስ ሀብት እንዲጣራ ሲሆን አመልካቾች ጣልቃ በመግባት ከ1ኛ-5ኛ ያሉት አመልካች በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ውስጥ የሚገኘው የቤት ቁጥር 109 የሆነው ውስጥ የተሰራው 5 ክፍል ቤት የ1ኛ አመልካች የግል ንብረት ነው፣ ግሮሰሪ ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች የውርስ ሀብት ተብሎ ሊካተቱ አይገባም የሚል ሲሆን 6ኛ እና 7ኛ አመልካቾች ደግሞ ሟች ሲያስሰተባብሩት የነበረውና ዕጣም ደርሷቸው ክፍያ የወሰዱበት ዕቁብ ውስጥ ያልተከፈላቸው ገንዘብ በውርስ ዕዳነት እንዲያዝ ተከራክረዋል፡፡ አቤቱታ የቀረበበት በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ውስጥ የሚገኘው የቤት ቁጥር 109 የሆነው ባለ አንድ ደጃፍ 3 ክፍል ቤት የ1ኛ አመልካች እና የሟች አማረ ተክሌ የጋራ ንብረት ሲሆን የሟች አማረ ግማሽ የውርስ ሀብት ድርሻ ሟች ፍስሃ አማረ ጨምሮ ከ2ኛ-5ኛ ያሉት አመልካቾች የጋራ ድርሻ ነው፤ የግማሽ ንብረቱ 1/5ኛ ድርሻ ለሟች ፍስሃ አማረ ልጆች ለሆኑት ለህጻን ቃልኪዳን ፍሰሀ አማረ፣ ህጻን ሚካኤል ፍሰሀ አማረ፣ ህጻን ናታኒም ፍሰሀ አማረ በውርስ የሚተላለፍ ንብረት ስለመሆኑ በውርስ አጣሪ ሪፖርት ተመላክቷል፡

ክርክር ያስነሳው 5 ክፍል ቤት የተሰራው በሟች አቶ ፍስሃ አማረ ወይስ በ1ኛ አመልካች የግል ገንዘብ የሚለውን የፍሬ ነገር ጭበጥ በመያዝ በሥር ፍርድ ቤት ማስረጃ ሰምቶ 5 ክፍል ቤቶች የተሰራው በሟች ፍስሃ አማረ የግል ገንዘብ ሳይሆን በ1ኛ አመልካች በመሆኑ 5 ክፍል ቤት በውርስ ንብረትነት ሊያዙ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ ይሕን በውሳኔ ክፍል ካመላከተ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት በንፋስ ስልክ ላፍቶ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 109 የሆነው ቤትና ይዞታ ግማሽ ድርሻ የ1ኛ አመልካች ሲሆን ግማሽ ድርሻው ውስጥ የሟች ፍስሃ አማረ 1/5ኛ ድርሻ ለተጠሪዎች ሊከፋፈል ይገባል ተብሎ ተወስኗል፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በሥር ፍርድ ቤት 5 ክፍል ቤት በውርስ ሀብትነት ሊያዝ አይገባም ተብሎ ከተወሰነ በኂላ እነዚህን 5 ክፍል ቤቶች ግንዛቤ ውስጥ ሳይሰገባ በቤት ቁጥር 109 የሚገኝና ቤትና ይዞታ ላይ የተጠሪዎችን ድርሻ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ነው፡፡

ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራቀኙ ክርክር በመነሳት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡ ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜም ምክንያትን ማስፈር እንደሚገባ በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 182(1) የተመለከተ ግዴታ ነው፡፡ ፍርድ በሚጻፍበት ጊዜ ስለጉዳዩ መግቢያ፣ በክርክሩ የተነሱትን ፍሬ ነገሮች ማስፈር፣ ምላሽ የሚያስፈልገውን የፍሬ ነገር ወይም የሕግ ጭብጥ መለየት፣ በተለየው ጭብጥ ማስረጃውን በመመዘን እና ተፈጻሚነት ያለውን ሕግ በመተግበር ለውሳኔው ምክንያትን በማስፈር ዳኝነት የተጠቀበትን ጉዳይ እልባት መሥጠትን ይጠይቃል፡፡ በዚህም ተከራካሪ ወገን በአግባቡ የተሰማ፣ ማስረጃው በአግባቡ ግምት ውስጥ የገባና ዳኛው ሕጉን እና የቀረበውን ማስረጃ መሠረት አድርጎ የወሰነው ስለመሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከ1ኛ-5ኛ ያሉት አመልካቾች እና ተጠሪዎች እያከራከረ የሚገኘው በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 109 የሆነው ውስጥ የሚገኙ አምስት ክፍል ቤቶች በማን የተሰሩ ናቸው የሚለውን የፍሬ ነገር ጭብጥ የሥር ፍርድ ቤት በመያዝ ማስረጃ ሰምቶ 5 ክፍል ቤቶች የተሰሩት በተጠሪዎች አውራሽ ሳይሆን በ1ኛ አመልካች ስለመሆኑ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ ፍርድ ቤቱ በውሳኔው ተራ ቁጥር 1 ላይ 5 ክፍል ቤቶች የሟች ፍስሃ አማረ የውርስ ንበረት አይደሉም ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ድምዳሜ እና ውሳኔ ላይ በተጠሪዎች በኩል ይግባኝ ቀርቦ ውሳኔው የተለወጠ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 109 የሆነው ውስጥ የሚገኙ 5 ክፍል ቤቶች በ1ኛ አመልካች የተሰሩና በሟች ፍሰሃ አማረ ውርስ ሀብትነት የሚካተቱ አለመሆኑ ከተወሰነ የሟች ፍሰሃ አማረ ድርሻ የሚሆነው በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ውስጥ የሚገኘው የቤት ቁጥር 109 በሆነው ቀድሞ የተሰራው ባለ አንድ ደጃፍ 3 ክፍል ቤት ውስጥ ባለው ድርሻ ልክ ሊሆን ይገባል፤ የቤት ቁጥር 109 ባለ አንድ ደጃፍ 3 ክፍል ቤት የ1ኛ አመልካች እና የሟች አማረ ተክሌ የጋራ ንብረት ሲሆን የሟች አማረ ግማሽ የውርስ ሀብት ድርሻ ሟች ፍስሃ አማረ ጨምሮ ከ2ኛ-5ኛ ያሉት አመልካቾች የጋራ ድርሻ ነው፤ የግማሽ ንብረቱ 1/5ኛ ድርሻ ለሟች ፍስሃ አማረ ልጆች ለሆኑት ለህጻን ቃልኪዳን ፍሰሀ አማረ፣ ህጻን ሚካኤል ፍሰሀ አማረ፣ ህጻን ናታኒም ፍሰሀ አማረ በውርስ የሚተላለፍ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ንብረት ነው። በሥር ፍርድ ቤት የተሰሩ የቤት ክፍሎች ሳይለይ የተጠሪዎችን የውርስ ድርሻ መወሰኑ 5 ክፍል ቤቶች በ1ኛ አመልካች ስለመሰራቱ በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠውን መሠረት ያላደረገና ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ግድፈት የተፈጸመበት ነው። የተጠሪዎች ድርሻ በቤት ቁጥር 109 ቀድሞ የተሰራው ባለአንድ ደጃፍ 3 ክፍል ቤት በመሆኑ በ1ኛ አመልካች የተሰራው 5 ክፍል ቤቶች በይዞታው ላይ ያረፉበት ካሬ ሜትር እና ቀድሞ የተሰራው ቤት ያረፈበት ቦታ መጠኑ ሳይለይ የተጠሪዎችን ድርሻ መለየት የማይቻል በመሆኑ ይሕ ፍሬ ነገር ሳይጣራ የተሰጠው ውሳኔ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል ብለናል።

በሌላ በኩል ላይ ከ1ኛ - 5ኛ ድረስ ያሉት አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡበት በግሮሰሪ ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች እና 6ኛ እና 7ኛ አመልካቾች የጠየቁት ያልተከፈለ የዕቁብ ገንዘብ በውርስ ዕዳነት ይያያዝልን ጥያቄ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ጭብጥ ሆኖ ያልተያዘ ከመሆኑም በላይ በስር ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ ተጣርተው የፍሬ ነገር ድምዳሜ የተደረሰባቸው በመሆኑና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን ያልተሰጠው ስለሆነ በዚህ ረገድ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል። ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል።

**ውሳኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 291703 ነሀሴ 10 ቀን 2014 ዓ/ም እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 116638 መጋቢት 28 ቀን 2014 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ለ) መሰረት ተሻሽሏል።

2. በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 109 በሆነው ቀድሞ የተሰራው ባለ አንድ ደጃፍ 3 ክፍል ቤት የ1ኛ አመልካች እና የሟች አማረ ተክሌ የጋራ ንብረት ሲሆን የሟች አማረ ግማሽ የውርስ ሀብት ድርሻ ሟች ፍስሃ አማረ ጨምሮ ከ2ኛ-5ኛ ያሉት አመልካቾች የጋራ ድርሻ ነው፤ የግማሽ ንብረቱ 1/5ኛ ድርሻ ለሟች ፍስሃ አማረ ልጆች ለሆኑት ለህጻን ቃልኪዳን ፍሰሀ አማረ፣ ህጻን ሚካኤል ፍሰሀ አማረ፣ ህጻን ናታኒም ፍሰሀ አማረ በውርስ የሚተላለፍ ድርሻ ነው በማለት ወስነናል።

3. በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 109 በሆነው በ1ኛ አመልካች ገንዘብ የተሰራው አምስት ክፍል ቤቶች የሟች ፍሰሃ አማረ የውርስ ሀብት ውስጥ ሊካተት አይገባም ተብሎ ተወስኗል።

4. ቀሪ የሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ክፍል ፀንቷል።

5. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 109 በሆነው ቤትና ይዞታ ላይ አስቀድሞ ተሰራው ባለአንድ ደጃፍ ሦስት ክፍል ቤት ያረፈበት ቦታ መጠን እና አምስት ክፍል ቤቶች የተሰራበት የቦታ መጠን በማጣራትና በመለየት

*ማ ስታወሻ፦ ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በፍርዱ በተመለከተው መሠረት የሚች ፍሰሃ አማረ የውርስ ሀብትን ለይቶ እንዲወሰን ጉዳዩን በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(2) መሰረት መልሠናል፡፡

6. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**<u>ትዕዛዝ</u>**

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*